# አሁን ስለ VCE እና VCAL ለማወቅ መመሪያ የት እንደሚገኝ?

## እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው ለሆኑ ተማሪዎችና ወላጆች መረጃ

State Government Victoria
Department of Education & Training

VICTORIAN CURRICULUM AND ASSESSMENT AUTHORITY

© 2006

## ስለ ቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCE)

ቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት (VCE) ምንድር'ነው?

ይህ VCE የምስክር ወረቀት ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በሚገባ ሲያጠናቁ የሚሰጥ ማረጋገጫ ነው። ይህ የምስክር ወረቀት በዓለም ዙሪያ ተቀባይነት ያለው የችሎታ ብቃት ይሆናል። በዩኒቨርሲቲ፣ ቴፍ ኮሌጅ (TAFE) እና በሥራ መስክ ለመሳተፍ VCE በበለጠ ለመማር የመሸጋገሪያ መንገድ ይሆናል። እንዲሁም በት/ቤት ውስጥ የሚሰጥ እና በርስዎ VCE ትምህርት ላይ የአፕረንቲሽፕ ወይም የስልጠና ትምህርትን ማካተት ይችላል።

### የ VCE (ቪክቶሪያ ትምህርት የምስክር ወረቀት) መቼ መጀመር እችላለሁ?

ይህ በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል ለመውሰድ የታቀደ ቢሆንም ከ10ኛ ክፍልም መጀመር ይቻላል። በቪክቶሪያ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ግማሽ የሚሆኑት አንዳንድ የ VCE ክፍሎችን ይወስዳሉ።

### የ VCE ትምህርት ፕሮግራም ምንድ'ነው?

ይህ የ VCE ትምህርትዎን ለማጠናቀቅ የሚቀርብ ፕሮግራም ነው።

ከብዙ የተለያዩ የ VCE ጥናቶች ውስጥ መምረጥ ይችላሉ።

### ምን ዓይነት ትምህርት መምረጥ አለብኝ?

በ VCE ውስጥ ለምምረጥ ከ90 በላይ የሚሆኑ የትምህርት ዓይነቶች ይገኛሉ። የነዚህ የትምህርት ዓይነት ዝርዝር ምዝገባ በገጽ 3 እና 5 ላይ ሊገኙ ይችላሉ። ከነዚህ ውስጥ 30 የሚሆኑት በVCE የሥራ ትምህርትና ስልጠና (VET) ፕሮግራሞች ሲሆኑ እንዲሁም በአገር አቀፍ ተቀባይነት ያለው ለኢንዱስትሪ የሙያ ብቃት የሚሆን ትምህርት ያቀርባል። ሌሎች ምርጫዎችም ይኖራሉ ለምሳሌ፥ በታሪክ ስለ አብዮት ኡደት ማጥናት ይችላሉ፣ የአውስትራሊያን ታሪክ ወይም የጣሊያንን የስነ-ፅሁፍና ስእል ማጥናት ይችላሉ። እንዲሁም ከብዙ የሂሳብ ትምህርት ወይም የጥናት ቡድን ወይም ለብቻ ሙዚቃ የማሳይት ትምህርት ዓይነቶችን መምረጥ ይቻላል። ከእንግሊዝኛ ባሻገር (LOTE) በ46 ቋንቋዎች ትምህርት ይኖራል።

የ VCE ትምህርት ለአንድ ዓመት የታቀደ ሲሆን እንዲሁም የተለያዩ ክፍሎች ይኖሩታል። አንድ ክፍል (unit) የግማሽ ዓመት ወይም ለአንድ ሰሚስተር/የትምህርት ፈረቃ ጊዜ ይወስዳል። ይኖሩታል። አንድና ሁለት ክፍሎች (Units) እንደ አንድ ክፍል አድርጎ መውሰድ ሲቻል - ይህም ክፍል 1 ወይም ክፍል 2 ሲባል - ነገር ግን ክፍል 3 እና 4 እንደ ሁለት ተከታታይ ክፍሎች ተደርጎ መውሰድ ይቻላል። በክፍል 3 ለመማር ከተመዘገቡ፣ በዚያኑ ዓመት የክፍል 4 እንደሚማሩ ይጠበቃል።

በአጠቃላይ የ VCE ፕሮግራም በሁለት ዓመት ውስጥ ከ20 እስከ 24 ክፍሎች ቢኖሩትም፣ ነገር ግን በአንድ ዓመት የሚወስዱት የክፍሎች ቁጥር ሊለያይ ይችላል።

በት/ቤትዎ ውስጥ የክፍል 3 እና 4ን በመጨረሻ ዓመት ላይ ይወስዳሉ። በ11ኛ ክፍል ሆኖ የተወሰነ ክፍል 3 እና 4 ለመውሰድ ካቀዱ እና የክፍል 1 እና 2 ከመውሰድ ባሻገር እነዚህን ከወሰዱ በበለጠ እንደሚያስቸግር አይዘንጉ።

በሚመርጡበት ጊዜ የሚከተለውን ግምት ውስጥ ማስገባት:

- እርስዎ ደስ የሚልዎን
- ጥሩ በሆኑበት መስክ
- ወደ ፈለጉት ሥራ ሊመራዎ የሚችል
- ባሰቡት መስክ ለበለጠ ስልጠና እና ለሶስተኛ ደረጃ ኮርስ ትምህርት ብቁ ሊያደርግዎ የሚችል።
- በ VCE ውስጥ እያሉ ለ VCE VET ፕሮግራም የሚያመራና የ VET ተቀባይነት ያለው ችሎታ ማግኘት የሚያስችል ይሆናል።

### ከት/ቤቴ ምን መምረጥ እችላለሁ?

እያንዳንዱ ት/ቤት በVCE ጥናት እና VCE VET ፕሮግራሞች ውስጥ ምን መስጠት እንዳለበት በመወሰን የራሳቸውን የጊዜ ሰንጠርዥ ይቀርቡላቸዋል።

የፈለጉትን የትምህርት ዓይነት በት/ቤትዎ በኩል መስጠት ካልቻለ፣ ከት/ቤትዎ ውጪ ተጨማሪ ጥናት ማካሄድ ይችላሉ (ለምሳሌ፥ ከቪክቶሪያ የቋንቋ ት/ቤት)።

በት/ቤትዎ የትኛው የ VCE ትምህርት እንደሚሰጥ ማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን የመረጡት ትምህርት ከት/ቤትዎ የጊዜ ሰንጠረዥ ጋር ተስማሚ መሆን አለበት።

### ለርቀት ትምህርት ማግኘት እችላለሁን?

ስለ የርቀት ትምህርት መረጃ ለማግኘት (ለመስጠትና ለመመዝገብ የሚፈቀዱ የትምህርት ዓይነቶች) በድረገፅ www.distance.vic.edu.au ላይ ይመልከቱ።

### በ VCE ፕሮግራም ላይ ምን ማካተት አለብኝ?

ትክክለኛ የክፍሎች ቁጥር ለመውሰድዎ እና በVCE ለመመረቅ ትክክለኛ የትምህርት ቅንብር ማድረግዎን ለማረጋገጥ በት/ቤትዎ በኩል ምክር ይሰጥዎታል። የመመዝገቢያ ቅጽዎን ለማስገባት እድል በመስጠትና በዓመቱ መጀመሪያ ላይ እንደተፈቀደልዎ በግልዎ ዝርዝር ማቅረቢያ ቅጽ ላይ ያረጋግጡ።

የ ምስክር ወረቅትዎን ለማግኘት ቢያንስ 16 ክፍሎችን በሚገባ ማጠናቀቅ አለብዎ።

በአጠቃላይ ምን ያህል ክፍሎችን ማካሄድዎ ሳይሆን፣ ነገር ግን በሚገባ ማጠናቀቅ አለብዎ:

- ከዚህ በታች ከተጠቀሱት የእንግሊዝኛ ክፍል ቢያንስ ሶስት ክፍሎችን ማጠናቀቅ:
  - ጀማሪ የእንግሊዝኛ ክፍሎች 1 እና 2
  - እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ (ESL) ክፍሎች/ Units 1 – 4
  - እንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍሎች/ Units 1 – 4
  - የጽሁፍ/Literature ክፍሎች/Units 1 – 4

በክፍሎች 1 እና 2 ላይ ለእንግሊዝኛ የሚያስፈልግ ከሁለት ክፍሎች በላይ አይሆንም። በአገር አቀፍ ሶስተኛ ደረጃ ለመግባት (ENTER) እድል ለማግኘት ሁለቱንም ክፍል/Unit 3 እና 4 የእንግሊዝኛ ተከታታይ ትምህርቶች ማጠናቀቅ አለብዎ።

- ከእንግሊዝኛ ቡድን ተከታታይ ጥናት ሌላ በተጨማሪ ሶስት ተከታታይ የክፍል 3 እና 4 ትምህርት ይመረጣል። እነዚህ ተከታታይ ጥናቶች ከ VCE ትምህርት እና/ወይም ከ VET ፕሮግራሞች ውስጥ ሊሆን ይችላል። በVTAC ምስክር ወረቀት ላይ ቦታ ለአንዳንድ የ VCE እና VET ትምህርቶች ለማዋሃድ እንደሚይፈቀድ ማወቅ ይገባዎታል። የVCE ትምህርት ሲያጠናቅቁ በአገር አቀፍ ለሶስተኛ ደረጃ ለመግባት (ENTER) ማመልከት ሲፈልጉ፣ እነዚህ ገደቦች መኖራቸውን ማወቅ ያስፈልግዎታል። ለ VCE አስተባባሪ ያነጋግሩ።

### ስለ የሙያ ትምህርትና ሥልጠና ምስክር ወረቀት (VET)

VCEን ከ VET ጋር ለማካተት ሶስት አማራጭ ሲኖሩ እንደሚከተለው ይሆናል።

### 1. VCE VET ፕሮግራም ምንድ'ነው?

የ VCE VET ፕሮግራም እንደ VCE አንዱ ክፍል ይቆጠራል። በ VCE VET ፕሮግራም በኩል እንደ ሌላው VCE ክፍለ ትምህርት የሚቆጠር የሥራ ምስክር ወረቀት ይሰጥዎታል። በ VCE VET ፕሮግራም በኩል የክፍል/Units 1–4 ክሬዲት ዋጋ ይሰጥዎታል። ይህ ማለት በተወሰነ የሥራ ስልጠና ትምህርት ለማካሄድ ሲችሉ፣ ለምሳሌ፣ ለመስተንግዶ፣ እርሻ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ወይም የኢንጂነሪንግ የስልጠና ትምህርት ናቸው።

ያለዎትን እውቀትና ችሎታ ተግባራዊ ለማድረግ እድል ያገኙ ዘንድ በሥራ ቦታ ላይ ተመድበው ለመማር እንዲያስችል እንደ አንዱ የስልጠና አካል ሆኖ ይቆጠራል።

በዚህ ስልጠና አማካኝነት የVCE ትምህርትዎን በሚገባ ለማጠናቀቅ አስተዋጽኦ ሲኖረው እንዲሁም የሥራ ችሎታዎ በአገር አቀፍ ተቀባይነት እንዲኖረው ይረዳል። በሥራ ችሎታዎ አማካኝነት በበለጠ ስልጠና እንዲያደርጉ ይረዳል። ለምሳሌ፣ ት/ቤት ከጨረሱ በኃላ ወደ ቴፍ/ TAFE ተቋም በመግባት የሥራ ማግኘት እድልዎን ያሰፋዋል።

እንዲሁም የትምህርት ነጥብ የሚያስገኙ ብዛት ያላቸው ፕሮግራሞች ሲኖሩ እነዚህ እና ለሎች እንደ VCE VET ፕሮግራሞች ENTER ለማግኘት አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ለመምረጥ የሚያስችሉ ከ30 በላይ የ VCE VET ፕሮግራሞች አሉ።

የእያንዳንዱ VCE VET ፕሮግራም ትንሽ መጽሐፍ በVCAA ቄብሳይት፥ www.vcaa.vic.edu.au ላይ ቀርቧል።

እንዲሁም የእነዚህ ትንሽ መጽሐፍ ፕሮግራም ቅጂ ት/ቤትዎ አለው።

ነብስወከፍ VCE VET ፕሮግራም እንዴት ለVCE ተመህርትዎ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ለት/ቤት VCE ወይም VET አስተባባሪ መጠየቅ ይችላሉ።

### 2. በት/ቤት ያለ አዲስ አፕረንቲስሽፕ ወይም ትራኒሽፕ (New Apprenticeship or traineeship) ማለት ምንድ'ነው?

በት/ቤት ያለ አዲስ አፕረንትስሽፕ (SBNA) ወይም ትራኒሽፕ አማካኝነት ለ VCE ትምህርት አስተዋጽኦ የማድረግ ሌላው መንገድ የሥራ ስልጠና ይሆናል። በአፕረንቲስ ስልጠና ለመውሰድ የሚከፈለው ሥራ እንዲኖርዎ ሲያስፈልግ፣ እንዲሁም በስለጠናና የሶስተኛ ደረጃ ትምህርት ጽ/ቤት (OTTE) በኩል መመዝገብና የኮንትራት ውል መፈረም ይኖርብዎታል።

የትርፍ - ሰዓት ሥራና ከሥራ ስልጠና ጋር ለማካሄድ የVCE ፕሮግራምዎ የጊዜ ድርሻ ይኖረዋል። ስለዚህ የርስዎ VCE ሶስት ክፍሎችን ይይዛል:

- የ VCE ጥናት በት/ቤት የሚወሰድ
- የሥራ ስልጠና በቴፍ/TAFE ተቋም የሚወሰድ፣ ለምሳሌ
- ስልጠና በሚያደርጉበት ኢንዱስትሪ ውስጥ የትርፍ ሰዓት፣ ክፍያ ያለው ሥራ ማካሄድ ናቸው።

በአሁን ጊዜ አስራ አንድ ኢንዱስትሪዎች ሲኖሩ በ VCE ክሬዲት ለማስገኘት የተቀናጀ VCAA ተቋቁሟል ስለዚህ እርስዎ የአፕረንትስሺፕ ወይም የትሬኒሽፕ እንደ VCE የክፍል ትምህርት የሚቆጠር መውሰድ ይችላል።

በSBNA ያገኙት ችሎታ እንደ VCE VET ፕሮግራም የVCE ትምህርትን በሚገባ ለማጠናቀቅ አስተዋጽኦ ሲኖረው፣ ይህም ለVCE ክፍል/Units 1-4 ክሬዲት/ነጥብ ያስገኛል። የSBNA ፕሮግራም እንደ VCE VET ፕሮግራም በ ENTER ላይ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

የርስዎ SBNA ፕሮግራም እንዴት መቀናጀት እንደሚችል በት/ቤትዎ በኩል ማረጋገጥ ይችላሉ።

እንዲሁም በVCE VET እና SBNA ፕሮግራሞች በኩል የተማሪ VCAL ትምህርት ፕሮግራም ክፍል መመስረት ይቻላል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በኃላ በVCAL በኩል ይብራራል።

### 3. በ VCE ውስጥ በጥቅሉ የሚታሰብ ክሬዲት/ነጥብ

ለሥራ ስልጠና የምስክር ወረቀት ለማውጣት ከፈለጉ በVCE VET ፕሮግራም በኩል አይሰጥም ወይም ከዚህ በላይ ባለው ይልክዎትና የሚወስዱት ስልጠና VCEን በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ ነጥብ ሊያስቆጥርልዎ ይችላል።

ይህን ነጥብ ማቀናጀት "ጥቅል ነጥብ" አያያዝ ተብሎ ይጠራል። VCE በሚያካሂዱበት ጊዜ ስለነጥብ አሰጣጥ በተመለከተ አንዳንድ ደንቦች አሉ። በበለጠ መረጃ ለማግኘት የ VET ወይም VCE አስተባባሪን ማነጋገር አለብዎ።

## VCEን እንዴት መጨረስ እችላለሁ?

ከዚህ የሚቀጥለው ክፍል VCEን ለመጨረስ እንዴት መሥራት እንደሚገባዎ ይገልጻል። እንዲሁም ስለሚካሄደው ፈተና፣ እንዴት የፈተና ውጤትዎ ሪፖርት እንደሚደረግልዎና በነዚህ ውጤቶች በኩል ማግኘት የሚችሉትን ጥቅሞች በዚህ ክፍል ማብራሪያ ይቀርባል።

### ለመጨረስ ምን ማድረግ አለብኝ?

በ VCE መመረቅ ማለት ያገኙት ጥሩ ውጤት በሞላው አውስትራሊያና በዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የምስክር ወረቀት እንዲኖርዎ ያስችልዎታል። ለመጨረስ የሚያስፈልጉት:

- ለVCE ፕሮግራም በሚጠይቀው ጥሩ ውጤት ማግኘት
- የርስዎ ሥራ ተገምግሞና ጥሩ ደረጃ ካለው ይሆናል።

### ታዲያ የደረጃ መለኪያውን እንዴት ላውቅ እችላለሁ?

ለመጨረስ በሚያስፈልጉት ፕሮግራም አንዴ ከመረጡ በኃላ፣ ለመጨረስ የሚያስችል ብቁ የሆነ የሥራ ውጤት ማቅረብ ያስፈልግዎታል። በወሰዱት የትምህርት ክፍሎች/units ላይ በጥሩ ሁኔታ ማጠናቀቅ የ VCE መጨረስን ይወስናል። በጥሩ ሁኔታ የተጠናቀቀ ክፍለ ትምህርት 'S' በሚል ይገለጻል። ለሚፈለገው በጥሩ ሁኔታ ያልተጠናቀቀ ክፍለ ትምህርት 'N' በሚል ምልክት ይገለጻል።

ስለ በጥሩ ሁኔታ ማጠናቀቅ ጉዳይ ማለት የትምህርተ ክፍሎች/Units 1 እና 2 ወይም ክፍሎች/Units 3 እና 4 ለማጠናቀቅዎ በት/ቤትዎ በኩል ይወሰናል።

እርስዎ ለእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት በቀረበው የጥናት እቅድ በሚያሳዩት ውጤት መሰረት በጥሩ ሁኔታ ለመጠናቀቁ ውሳኔ ይሰጥበታል። የክፍለ ትምህርቱን በሚያጠናቅቁበት ጊዜ ምን ለማወቅ እንደሚጠበቅብዎና ማድረግ እንደሚችሉት (ቁልፍ በሆኑ እውቀትና ችሎታ) በዚህ ውጤት በኩል ይገለጻል። እያንዳንዱ የVCE ትምህርተ ክፍል ውጤቶች በሁለትና አራት መካከል ይሆናል።

ስለመረጡት ክፍለ ትምህርት በሞላ በጥሩ ሁኔታ ለማጠናቀቅዎ በት/ቤትዎ በኩል ይወሰናል። እንዴት እድገት እንዳሳዩ ለማመልከት እንዲያስችለው ት/ቤትዎ ለዚህ ውሳኔ አሰጣጥ የማወዳደሪያ ተግባራትን ያወጣል። በት/ቤት ውስጥ በተመዘገቡ የጥናት ንድፍ መሰረት እነዚህ ተግባራት በአስተማሪዎ በኩል ይወሰናሉ። ስለተግባር ዝርዝራቸውንና የሚያስረክቡበትን የመጨረሻ ቀን በአስተማሪዎ በኩል ይሰጥዎታል። የሚያስረክቡበትን ቀን ገደብ ለማራዘም ብቁ ምክንያት ማቅረብ አለብዎ። ይሁን እንጂ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከአንዴ በላይ ካራዘሙ በቀጣዩ የሚያቀርቡት ሥራ ተጠናቆ በተባለው ቀን እንዲቀርብ እቅድ እንዲያወጡ ያስፈልጋል። ት/ቤት በወሰነው ቀን አለማስረከብ ማለት ክፍለ ትምህርቱን በብቃት እንዳላጠናቀቁ ተደርጎ ይቆጠራል።

ለክፍል/Units 1 እና 2, በአጠቃላይ ት/ቤቶች 'S' ወይም 'N' በሚለው ያተኩራሉ (ይሁን እንጂ አንዳንድ ት/ቤቶች የሥራ ውጤትዎን በሚያሳዩበት ጊዜ ያገኙትን የክፍል ውጤት ነጥብ/ደረጃ ሪፖርት ማድረግ ይችሉ ይሆናል)።

## ለክፍልUnits 3 እና 4 እንዴት ማሳወቅ እችላለሁ?

ለክፍል/Units 3 እና 4፣ የክፍል ውጤት ነጥብ/ደረጃ ሲያገኙ እንዲሁም ከዚህ በላይ የተጠቀሰውን 'S' ወይም 'N' ያገኛሉ። በክፍል/Units 3 እና 4 ደረጃ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች VCAA ይቆጣጠራል።

የክፍል ውጤት ነጥብ/ደረጃ ግምገማ በፈተና ወይም በክፍል ውስጥ የሚደረግ ግምገማ ይሆናል። እያንዳንዱ የ VCE ጥናት በክፍል/Units 3 እና 4 ተከታታይ ትምህርት ላይ ሶስት የክፍል ውጤት ደረጃዎች ሲኖሩት፣ ይህም በሁለት የት/ቤት ግምገማ ወይም በአንድ ፈተና ወይም በአንድ የት/ቤት ግምገማ ወይም በሁለት ፈተናዎች ይሆናል። ተመሳሳይ በሆነ የግምገማ መንገድ ለ VCE VET ፕሮግራሞች በት/ቤት ግምገማ እና በፈተና አማካኝነት ነጥብ ይሰጣቸዋል። እያንዳንዱ የVCE ትምህርት ቢያንስ አንድ ፈተና ይኖረዋል።

በ VCE ሁለት ዓይነት የት/ቤት ግምገማ ይኖራል።

የመጀመሪያው በት/ቤት-የሚጠና የኮርስ ሥራ ይባላል። በግምገማ ተግባር ላይ ምን ያህል ጥሩ እንደሠሩ በዚህ ይጠናል። እነዚህ ተግባራት በአብዛኛው በክፍል ጊዜ ላይ ይደረጋል። ከስቱዲዮ ሰነ-ጥበባት በስተቀር በት/ቤት-የሚጠና የኮርስ ሥራን ያካተተ ሁሉም ጥናቶች ይሆናሉ።

ሁለተኛው የት/ቤት ግምገማ ዓይነት ደግሞ በት/ቤት-የሚጠና ተግባር ይሆናል። በዚህ በት/ቤት-የሚጠና ተግባር ሰባት ጥናቶች ብቻ ሲኖሩ፣ ስነ-ጥበብ፣ የንድፍና ቴክኖሎጂ፣ የምግብና ቴክኖሎጂ፣ ሚዲያ፣ ስቱዲዮ ስነ-ጥበባት፣ የኢንጂነሪንግ ዘዴዎች እና እየተያዩ ግንኙነት መፍጠርና የንድፍ አወጣጥ ይሆናል። በት/ቤት-ለሚጠና ተግባር የሚያስፈልጉ ነገሮች ለሁሉም ት/ቤቶች አንድ ዓይነት ሲሆኑ በ VCAA ይወሰናል። ት/ቤትዎ በሚያስፈልጉ እንቅስቃሴዎች ላይ ንድፍ በማውጣት በት/ቤት-ስለሚጠና ተግባር ሥራ እንዲጠናቀቅ ይረዳል። ነጥብና የክፍል ደረጃዎች እንዴት እንደሚሰጥ በVCAA በኩል ይወሰናል። አስተማሪዎ ሲያርምልዎ ት/ቤትዎ ደግሞ ምን ያህል በት/ቤት-ስለሚጠና ተግባር እንደሠሩ የሚገልፅ በVCAA በኩል ነጥብ ይላክልዎታል።

### በውጪ የሚሰጡ ፈተናዎች

ከት/ቤት ውጪ የሚቀርብ ፈተና (የፅሁፍ፣ የቃል፣ የቲያትር ሥራ ወይም የኤሌትሮኒክ) በ VCAA በኩል ይዘጋጅና ይታረማል። አብዛኞቹ በህዳር/November ወር ሲሰጡ ነገር ግን ጥቂት የትምህርት ጥናቶች በሰኔ/June ወይም ጥቅምት/October ወር ውስጥ ይሰጣሉ።

### በ VCE ግምገማ ላይ ምን መፈተሽ አለበት?

በሞላው የመስተዳድር ክልል ውስጥ ተመሳሳይ የእርማት ደረጃ መኖሩን ለማረጋገጥ ሁለቱም ማለት በት/ቤት ግምገማና ፈተናዎች ላይ VCAA ጥንቃቄ የተሞላበት አሠራር ስልት አለው። ይኖረዋል። በእያንዳንዱ የግምገማ ጉዳይዎ ላይ የስታቲስቲካል አሠራሮችና ብዛት ያለው ማጣሪያዎችን ያስገባሉ። ዝርዝር ሁኔታ በት/ቤትዎ በኩል ወይም በVCAA ዌብሳይት ላይ ማግኘት ይችላል።

## የጠቅላላ ግኝት/መግቢያ ፈተና/ (GAT) ምን ማለት ነው?

ይህ GAT የአጠቃላይ እውቀትና ችሎታ መመዘኛ ፈተና ሲሆን ይህም በጽሁፍ ግንኙነት መፍጠር፣ የሂሳብ ትምህርት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ የሰብዓዊ፣ የስነ-ጥበባትና የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርት ይሆናል።

ለ VCE ግምገማ አሠራር ዘዴዎች የጠቅላላ ግኝት ፈተና (GAT) ጠቃሚ የሆነ ክፍል ነው። ምንም እንኳን VCEን ለመጨረስ ከሚያስፈልገው አንዱ ክፍል ባይሆንም እንዲሁም በVCE ወይም በ ENTER ማስገቢያ ውጤት ላይ ባይቆጠርም፣ በት/ቤትዎ ግምገማ እና ፈተና በትክክል እንዲታይ ጠቅላላ ግኝት ፈተና (GAT) በማረም ላይ ጠቃሚ የሆነ የሥራ ድርሻ ይኖረዋል።

ስለዚህ በማንኛውም ክፍል/Units 3 እና 4 የ VCE ትምህርት ወይም VCE VET ነጥብ ፕሮራም ላይ ከተመዘገቡ - በ11ኛ ክፍልም ሆነ 12ኛ - በ VCAA በኩል ነጻ ካልሆኑ በስተቀር ለ GAT ፈተና መቀመጥ አለብዎ። ለዚህ ብቁ ምክንያት ማቅረብ አለብዎ።

ያገኙት የGAT ውጤቶች ከጽሁፍ ማብራሪያ ጋር ሪፖርት ይደረጋል።

## ያገኘሁት ውጤት እንዴት ሪፖርት ይደረግልኛል?

### ውጤት በሚገልጽ ጽሁፍ

የክፍል/ Units 1 እና 2 ብቻ የሚወስዱ ከሆነ በት/ቤትዎ አማካኝነት ውጤት የሚገልጽ ጽሁፍ ይደርስዎታል። የክፍል/ Units 3 እና 4 የሚወስዱ ከሆነ በታህሳስ/December ወር በ VCAA አማካኝነት ውጤት የሚገልጽ ጽሁፍ በፖስታ ይላክልዎታል።

በውጤት መግለጫው ጽሁፍ አማካኝነት እርስዎ በተመዘገቡበት – በክፍል/Units 1, 2, 3 እና 4 እያንዳንዱ ክፍል 'S' ወይም 'N' ማግኘትና አለማግኘትዎ ይገለጻል።

በት/ቤትዎ - የሚጠና ኮርስ ሥራ፣ በት/ቤትዎ - የሚጠና ተግባራትና ፈተናዎች ከ A+ እስከ E ወይም UG (ደረጃ የሌለው/ungraded) በሚል ሪፖርት ይደረጋል።

ሁለት ወይም ከዚህ ደረጃ በላይ ከተገመገመ እና ለሁለቱም 'S' ማለት ክፍል/ Units 3 እና 4 ካመጡ የጥናት ነጥብ ያገኛሉ። የጥናት ነጥቡ የሚሰላው ከ0-50 ባለ መለኪያ ነጥብ ሲሆን እንዲሁም ትምህርቱን ከወሰዱት ሌሎች ተማሪዎች ጋር በማወዳደር ምን ያህል ጎበዝ እንደሆኑ ማመዛዘን ይቻላል።

ይህ የጥናት ነጥብ በVCAA በኩል ስሌት ሲካሄድ በቪክቶሪያ ሶስተኛ ደረጃ መመዝገቢያ ማእከል (VTAC) የርስዎን ENTER አቅም ለማስላት ይሆናል (ከዚህ በታች ያለውን 'ማወቅ የምፈልገው ሌሎች ነገሮች' የሚለውን ማየት)።

የVCE VET ክፍሎችን ካጠናቀቁ በኃላ በውጤት ማቅረቢያ ጽሁፍዎ ላይ ይታያሉ። እንዲሁም ሙሉ የVCE VET ፕሮግራም ካጠናቀቁ በኃላ ካለዎ VCE በተጨማሪ በእውቅና ካለው የስልጠና ድርጅት (RTO) በኩል ለየት ያለ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ። በVCE VET ፕሮግራም የጥናት ነጥብ ግምገማ ካካሄዱ ያገኙት ነጥብ ከ VCE ጥናት ጋር ሆኖ በውጤት ማቅረቢያ ጽሁፉ ላይ ይካተታል።

## VCE የምስክር ወረቀት

እንዲሁም VCE ለመጨረስ አስፈላጊ የሆኑ ጥናቶችን በሚገባ ካጠናቀቁ የምስክር ወረቀት ያገኛሉ።

# ማወቅ ያለብኝ ሌሎች ነገሮች

## የተጨማሪ ጊዜ ትምህርት (Extension studies)

እነዚህ ትምህርተ ጊዚያት ከ VCE ጋር የሚወሰዱ የዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዓይነቶች ናቸው። እርስዎ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ ከሆነና በተጨማሪ ለመሥራት ሲፈልጉ፣ ካሉበት VCE ደረጃ በላይ የትምህርት ዓይነት ለማስፋት ጥሩ ዘዴ ናቸው። እነዚህ የVCE ክፍሎች አይደሉም፣ እንዲሁም VCEን በሚገባ ለመጨረስ ከሚያስፈልጉት 16 ክፍሎች ውስጥ ሊቆጠሩ አይችሉም።

### የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜን ማን ማካሄድ ይችላል?

ይህ ትምህርት ከፍተኛ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎች ይሆናል። በየዓመቱ 2 ከመቶ የሚሆኑት VCE ተማሪዎች ይፈቀድላቸዋል። ለዩኒቨርሲቲ በቀጥታ አመልካች ተማሪዎች በመረጡት ትምህርት ይቀርብላቸዋል። ተማሪዎች ለተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ከመጀመራቸው በፊት ት/ቤታቸውን ማማከር ይኖርባቸዋል። በዩኒቨርሲቲዎች የተመረጡ ተማሪዎች የVCE እና የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራምን ማጠናቀቅ ይችሉ ዘንድ ለማረጋገጥ ት/ቤትዎ በዩኒቨርሲቲ የወጣ መመሪያ ይኖረዋል። የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራሞች በመጀመሪያ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ፕሮግራም ቢያንስ 20 ከመቶ የሙሉ ቀን ትምህርት ናቸው።

በፈለጉት ተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራም ለመሳተፍ በVCE ዝግጅት ትምህርት ላይ ግኝትዎ ለምርጫ ቁልፍ ይሆናል። በተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራምዎ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ዓይነትን ለመምረጥ የቅድመ ዝግጅት ትምህርት ጠቃሚ የሆነ መረጃ ይሰጥዎታል። በቅድመ ዝግጅት ትምህርት ላይ ክፍል/Unit 3 እና 4 በተከታታይ መጨረስ ሲገባዎ ይህም በዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዓይነት ለመጀመር ጠቃሚ መንደርደሪያ ይሆናል። አንዳንድ ቅድመ ዝግጅት ትምህርት ከተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ጋር አብሮ በተመሳሳይ ጊዜ መውሰድ ይቻላል። ይህን በተመለከተ ከት/ቤቱና ዩኒቨርሲቲው ምክር ያስፈልግዎታል። እንዲሁም በVCE ትምህርት ነጥብ ቢያንስ 41 በቅድመ ዝግጅት ትምህርት ላይ ጥሩ ወጤት ስለማገኘትዎ ት/ቤትዎ ማመን አለበት። (ስለ ትምህርት ነጥብ መረጃ ለማገኘት 'ያገኘሁት ውጤት እንዴት ሪፖርት ይደረገልኛል?' / 'How are my results reported to me?' የሚለውን ይመልከቱ።

### ጥቅሞቹ ምንድ'ናቸው?

የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜዎን በሚገባ ካጠናቀቁ በውጤት ማቅረቢያ ጽሁፍ ላይ ሪፖርት ሲደረግ ይህም ለርስዎ ENTER ማስገቢያ ላይ እንደ ስድስት VCE ትምህርት በምቁጠር አስተዋጽኦ ይኖረዋል። በተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ በሚያገኙት ውጤት መሰረት የርስዎን ENTER ማጠቃለያ ሲታሰብ በተጨማሪ 4.0፣ 5.0 ወይም 5.5 points /ነጥቦችን ለማስገኘት ይችል ይሆናል። የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራምን ካለፉና በዩኒቨርሲቲ የዚህ ትምህርት ዓይነት ያለው ኮርስ ከመረጡ በሁለተኛ ዓመት ደረጃ ሊታሰብልዎ ይችላል።

ያስተውሉ፣ ለተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ሲመዘገቡ ሥራ እንደሚበዛና ከፍተኛ ሥራ እንደሆነና ነገር ግን የሚያገኙትም ታላቅ ሽልማት ይሆናል።

ታዲያ ይህ ፕሮግራም ለርስዎ ይሆናል ካሉ፣ እባክዎ ዩኒቨርሲቲው ስለሚያቀርበው የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ዝርዝር ሁኔታ ለማወቅ ዩኒቨርሲቲዎችን በቅድሚያ ያነጋግሩ። በእያንዳንዱ ዩኒቨርሲቲ የሚቀርብ የትምህርት ዓይነት በየዓመቱ ሊቀየር ስለሚችል ታዲያ በተጨማሪ ትምህርተ ጊዜ ፕሮግራም ላይ ለመመዝገብ ሲወስኑ ይህን መገንዘብ ጠቃሚ ይሆናል።

## ዩኒቨርሲቲ ወይም ቴፍ/TAFE ውስጥ እንዴት መግባት እችላለሁ?

በእያንዳንዱ ጥናት ላይ ከሶስት ደረጃ ማወዳደሪያዎች ላይ VCAA የርስዎን የትምህርት ነጥብ ውጤት ያሰላል። ለእያንዳንዱ ትምህርት ከፍተኛው ነጥብ 50 ይሆናል።

በ VCAA የተሰሉ የትምህርት ነጥቦችን ለክፍል/Units 3 እና 4 በመጠቀም፣ VTAC የርስዎን ENTER መግቢያ ሊወስን ይችላል። በርስዎ ENTER የመግቢያ ስሌት የሚጠቀሙ ሌሎች ጥናቶች እንደ VCE VET ፕሮግራሞች እና የተጨማሪ ትምህርተ ጊዜን ያካተተ ይሆናል። 50 ከመቶ ለሚሆኑ ኮርሶች ለመምረጥ ENTER መግቢያ እንድ መጀመሪያ ምንጭ ይጥቅማል። ለቀሩት የኮርስ አመራረጥ ሥልጣን የተለያዩ ነጥቦች ሲኖሩት ይህም በ ENTER መግቢያ እና የጽሁፍ አቀራረብ፣ የቲያትረኛ/ሙዚቀኛ ችሎታ ፈተና፣ ቃለመጠይቅ ወ.ዘ.ተ ያካተተ ይሆናል። ENTER መግቢያ፣ ይህ ተማሪዎች በሚያካሂዱት ትምህርት ላይ በማወዳደርና በስታትስቲክ የተደገፉትን የትምህርት ውጤት ነጥቦች ወደ ENTER የትምህርት ዓይነት መግቢያ ነጥቦች በመቀየር ይሆናል። ይህ ማለት ሁሉም ትምህርት አብሮ በእኩልነት ለማጠቃለል እንዲያስችል እና ከዚያም ወደ ENTER መግቢያ ይቀየራል። ስለዚህ አሠራርና ለሶስተኛ ደረጃ አመራረጥ በተመለከተ የበለጠ ዝርዝር በሚከተለው VTAC ጽሁፎች ላይ ቀርቧል:

*Enter into Tertiary Study* (VTAC በዌብሳይት ብቻ)

*ABC of Scaling* (በታህሳስ/December ወር ከENTER ጽሁፍ ጋር ቅጅው ይላካል)

*Choice!* (በሞላው ት/ቤት ለ10ኛ ክፍል ትንሽ መጽሐፍ ይቀርባል)

*VTAC Guide 2007* (በጋዜጣዎች ይቀርባል)

Victorian Tertiary Entrance Requirements (VICTER) 2008 ወይም 2009 (በሞላው ት/ቤት ለ10ኛ ክፍል ትንሽ መጽሐፍ ይቀርባል)

VTAC ዌብሳይት: www.vtac.edu.au

## በVCE ስኬት እውቅና ማግኘት

ተማሪዎች ያላቸውን ጥረትና ተሰጥኦ ለማሳየት በ VCE ብዙ መንገዶች አሉ። ተማሪዎች በት/ቤትና በማህበረሰቡ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ በ VCE Achievers Award/ሽልማት አግኝዎች አማካኝነት እውቅና ይኖረዋል። በየዓመቱ በተማሪዎች የሚቀርቡ ጥሩ ሥራዎች በ VCE Season of Excellence/ የወቅቱ ጥሩ ሥራ አማካኝነት እውቅና ሲኖረው ይህም ምርጥ ንድፍ፣ ምርጥ ድርጊቶችና ምርጥ ስነ-ጥበባትን ያካተተ ይሆናል። እንዲሁም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሽልማቶች፣ VCAA ተራ እንግሊዝኛ ተናጋሪ ሽልማት እና የአውስትራሊያ ተማሪዎች ሽልማት የሚባሉ አሉ።

በነዚህ ሽልማቶች ላይ በበለጠ መረጃ ለማግኘት በሚከተሉት VCAA ዌብሳይት ላይ ያረጋግጡ:

www.vcaa.vic.edu.au/excellenceawards/seasonofexcellence/index.html

www.vcaa.vic.edu.au/excellenceawards/vceachiever.html

www.vcaa.vic.edu.au/excellenceawards/australianstudentprize.html

www.vcaa.vic.edu.au/excellenceawards/premiersaward.html

www.vcaa.vic.edu.au/excellenceawards/plainenglishspeaking/index.html

## ስለ VCAL በተመለከተ (ABOUT THE VCAL)

ለበለጠ መረጃ ለማግኘት VCAL የሚለውን በVCAA ዌብሳይት፣
www.vcaa.vic.edu.au/vce/publications/WhereToNow/vcallote.html ላይ መጫን ነው።